የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ-ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 58
ADDIS ABABA- 2nd August, 2004

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፫/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ........ ገጽ ፪ሺ፰፻፩

**CONTENTS**

PROCLAMATION NO- 413/2004

A PROCLAMATION TO AMEND THE QUALITY AND STANDARDS AUTHORITY OF ETHIOPIA ESTABLISHMENT PROCLAMATION page No. 2801

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፫/፲፱፻፺፮

## የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አ ዋ ጅ

የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፫/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ማሻሻያ

የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፪/፲፱፻፺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

## PROCLAMATION NO 413/2004

## A PROCLAMATION TO AMEND THE QUALITY AND STANDARDS AUTHORITY OF ETHIOPIA ESTABLISHMENT PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the Quality and Standards Authority of Ethiopia Establishment Proclamation;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Quality and Standards Authority of Ethiopia Establishment (Amendment) Proclamation No.413/2004.

2. **Amendment**

The Quality and Standards Authority of Ethiopia Establishment Proclamation No.102/1998 is herby amended as follows:

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተተክቷል፤

«፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል።»

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፯፣ ፰፣ ፱ እና ፲ ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፯፣ ፰፣ ፱ እና ፲ ተተክተዋል፤

«፯. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ

፩/ የደረጃዎችና የሰርቲፊኬሽን ካውንስል /ከዚህ በኋላ 'ካውንስል' እየተባለ የሚጠራ/፣

፪/ በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዲሬክተር፣

፫/ እንዳስፈላጊነቱ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ምክትል ዋና ዲሬክተሮች፣ እና

፬/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

፰. <u>የካውንስሉ አባላት</u>

የካውንስሉ ሰብሳቢና አባላት በመንግሥት ይሾማሉ፤ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፱. <u>የካውንስሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

ካውንስሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ባለሥልጣኑ አዘጋጅቶ በሚያቀርባቸው ብሔራዊ የጥራትና የደረጃዎች ፖሊሲና ስትራተጂ ሃሳቦች ላይ ይመክራል፤ በመንግሥት ሲፀድቁም ለአፈጻጸማቸው የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤

1/ Sub-Article (2) of Article 3 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2) The Authority shall be accountable to the Ministry of Trade and Industry."

2/ Article 7,8,9 and 10 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Articles 7,8,9 and 10:

"7. **<u>Organization of the Authority</u>**

The Authority shall have:

1) a Standards and Certification Council (hereinafter referred to as the 'Council')

2) a Director General to be appointed by the Government;

3) Deputy Director General to be appointed by the Minister of Trade and Industry as may be necessary; and

4) the necessary staff.

8. **<u>Members of the Council</u>**

Members of the Council including the Chairperson shall be appointed by the Government, and their number shall be determined as may be necessary.

9. **<u>Powers and Duties of the Council</u>**

The Council shall have the powers and duties to:

1) deliberate on national quality and standardization policy and strategy proposals of the Authority and, upon their approval by the Government, issue directives necessary for their implementation;

፪/ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ያፀድቃል፣

፫/ ለሠርቲፊኬሽን ሥራ ተፈጻሚነታቸው አስገዳጅ የሆኑ የምርት ውጤቶች፣ የሥራ ሂደቶችንና የአሠራር ሥርዓቶችን ደረጃዎች ይወስናል፣

፬/ በአገር ውስጥ ለሚሠሩ የጥራት ሠርቲፊኬሽን አካሎች፣ የኢንስፔክሽን አካሎች፣ የፍተሻ ላቦራቶሮች፣ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮችና ከነዚህ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ብቃት ላላቸው ባለሙያዎች እውቅና እንዲሰጥና እንዲመዘገቡ ይፈቅዳል፣

፭/ እንዳስፈላጊነቱ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ አባላቱን ይሰይማል፣ ከኮሚቴው በሚቀርብለት የቴክኒክ ግምገማ ሪፖርት ላይ ይወስናል፣

፮/ ለጥራት ማኅተምና ባለሥልጣኑ ለሚሰጣቸው ሌሎች አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን ተመን ያፀድቃል::

፲. <u>የካውንስሉ ስብሰባ</u>

፩/ ካውንስሉ መደበኛ ስብሰባውን በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ ያደርጋል፣ ሆኖም እንዳስፈላጊነቱ በሰብሳቢው ወይም ከአንድ ሶስተኛው ባላነሱ አባላቱ ሲጠየቅ በማናቸውም ጊዜ ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

፪/ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከካውንስሉ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል::

፫/ የካውንስሉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ የድምጽ አሰጣጡ እኩል በእኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ካውንስሉ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::»

2) approve Ethiopian Standards;

3) determine standards of products, processes and systems which shall be subject to mandatory certification;

4) authorize the recognition and registration of quality certification bodies, inspection bodies, testing laboratories, calibration laboratories and qualified personnel related to these activity areas operating locally;

5) establish, as may be necessary, a technical advisory committee, designate its members and decide on technical evaluation reports of the committee;

6) prescribe fees to be charged by the Authority for quality marks and other services.

10. <u>Meetings of the Council</u>

1) The regular meetings of the Council shall be held once every three months; provided, however, that extra-ordinary meetings of the Council may be called by the Chairperson or upon the request of at least one third of its members.

2) There shall be quorum where more than half of the members of the Council including the Chairperson are present at a meeting of the Council.

3) Decisions of the Council shall be made by majority vote and, in case of a tie, the Chairperson shall have a casting Vote.

4) Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure."

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ውስጥ «ዋና ሥራ አስኪያጅ» እና «ቦርድ» የሚሉት ተሰርዘው እንደ ቅደም ተከተላቸው «ዋና ዲሬክተር» እና «የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር» በሚሉት ተተክተዋል::

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



3/ The references to the “General Manager” and “Board” under Article 11 of the Proclamation are deleted and replaced by “ Director General” and “Ministry of Trade and Industry” respectively.

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of August, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF EHTIOPIA**